የሰበር መ/ቁ 24576

ቀን ሰኔ 20 ቀን 1998

ዳኞች፦ 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፦ የኢ.ት. መንገዶች ባለሥልጣን ጅማ ዲስትሪክት አልቀረበም።

መልስ ሰጪ፦ ዝናቧ አበበ ቀረበች።

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ የክስ ምክንያት /cause of action/ አለው? ወይምስ የለውም? የሚለውን የሕግ ነጥብ የሚመለከት ነው።

የም/አርሚያ አሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ መ/ሰጭ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡትን ክስ በመቀበል አከራክሮ ውሣኔ ሰጥቷል። በውሣኔው ላይ ይግባኝ የቀረበለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ከላይ የተመለከተውን የሕግ ነጥብ ሳይመረመር አልፎታል።

አመልካች በዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መ/ሰጭ መልስ ሰጥቷል።

ችሎቱም ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ የክስ ምክንያት /cause of action/ አለው? ወይስ የለውም? የሚለውን የሕግ ነጥብ መሠረት በማድረግ አቤቱታ ያቀረበበትን ውሣኔ መርምሯል።

ይህ ችሎት በመ/ቁ 16273 ጥቅምት 22 ቀን 1998 በሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕጉን ድንጋጌዎች በመተርጎም አንድ ሠራተኛ ከውሉና ከአሠሪና ሠራተኛ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ____ ቀን 26/10/98

ሕጉ አንፃር ሊያገኘው የሚገባና የቀረበለት ጥቅም ካለ የቀረበት ጥቅም እንዲሰጠው መጠየቅ /ክስ ማቅረብ/ የሚችል ሲሆን ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ ይወሰንልኝ ብቻ የሚቀርብን ክስ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድም ሆነ የሥራ ክርክር ችሎት ተቀብለው ሊያዩ የሚችሉበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።

በዚህ ጉዳይም የም/አ/አሰሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ መ/ሰጭ ያቀረቡትን ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡትን ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ውድቅ ማድረግ የነበረበት ሲሆን ጉዳዩን ተቀብሉ በማከራከር ውሣኔ በመስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል።

## ው ሣ ኔ

የም/አ/የአሠሪና ሠ/ወ/ቦ በመ/ቁ ጂ/ቢ/አም 2-49/2604 የሰጠው ውሣኔና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 38278 የሰጠው ትዕዛዝ /ውሣኔ/ ተሽሯል።

ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ________ ቀን 26/10/98